የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፴፬
አዲስ አበባ — ሰኔ ፳፱ ቀን ፲፱፻፹፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No. 34
ADDIS ABABA - 6th July, 1996

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፵፬/፲፱፻፹፰ ዓ.ም.
የኢትዮ—ቻይና የንግድ ፡ የኢኮኖሚና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ............................ ገጽ ፪፻፶፰

## CONTENTS

Proclamation No. 44/1996
Ethio-Chinese Trade, Economic and Technical Co-operation Agreement Ratification Proclamation ............................................ Page 258

## አዋጅ ቁጥር ፵፬/፲፱፻፹፰

### የኢትዮ—ቻይና የንግድ ፡ የኢኮኖሚና የቴክኒክ ትብብር ስምምነትን ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቻይና ሕዝባዊ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የተደረገው የንግድ ፡ የኢኮኖሚና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት ግንቦት ፭ ቀን ፲፱፻፹፰ አዲስ አበባ ላይ የተፈረመ ስለሆነ ፤

ስምምነቱ በሥራ ላይ የሚውለው ከጸደቀበት ዕለት ጀምሮ እንደሚሆን በስምምነቱ ውስጥ ስለተመለከተ ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፱ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት ከዚህ እንደሚከተለው ታውጇል ።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የኢትዮ—ቻይና የንግድ ፡ የኢኮኖሚና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፵፬/፲፱፻፹፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· <u>ስምምነቱ ስለመጽደቁ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቻይና ሕዝባዊ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል ግንቦት ፭ ቀን ፲፱፻፹፰ አዲስ አበባ ላይ የተፈረመው የንግድ ፡ የኢኮኖሚና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት ጸድቋል ።

## PROCLAMATION NO. 44/1996

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE ETHIO-CHINESE TRADE, ECONOMIC AND TECHNICAL COOPERATION AGREEMENT

WHEREAS, the Agreement on Trade, Economic and Technical Cooperation between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the People's Republic of China was signed in Addis Ababa on the 13th day of May, 1996;

WHEREAS, it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall enter into force as of the date of its ratification;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 6th day of July, 1996;

NOW, THEREFORE, in accordance with Aritcle 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Ethio-Chinese Trade, Economic and Technical Cooperation Agreement Ratification Proclamation No. 44/1996."

2. *Ratification of the Agreement*

The Ethio-Chinese Agreement on Trade, Economic and Technical Cooperation signed in Addis Ababa on the 13th day of May, 1996 is ratified.

፫· <u>የሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ሥልጣን</u>

የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር ፣ የንግድና የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ፣ የኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ባለሥልጣንና በስምምነቱ የተካተቱ የትብብር መስኮች የሚመለከቷቸው ሌሎች የፌዴራል አስፈጻሚ አካላት በየሥራ መስካቸው ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቷቸዋል ።

፬· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፱ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፱ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

3. *Power of Concerned Executive Organs*

The Ministry of Economic Development and Cooperation the Ministry of Trade and Industry, the Ethiopian Investment Authority and other federal executive organs concernd with the fields of cooperation included in the Agreement are hereby empowered to implement the Agreement with regard to their respective fields of activity.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 6th day of July, 1996.

Done at Addis Ababa, this 6th day of July, 1996.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ ።
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRIS